# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 ፣የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 11 ሐምሌ 24 2000 ዓ.ም

አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !

## የሰላም ጠባቂ ሃይሉ ተልእኮ እንዲያበቃ ተወሰነ

### በኢትዮ- ኤርትራ ድንበር ዙሪያ የጦርነት ስጋት እያየለ ነው

የአልጀርሱን ስምምነት ተከትሎ ላለፉት 7 አመታት በኢትዮ-ኤርትራ አወዛጋቢ ድንበር ሰፍሮ የነበረው የመንግስታቱ ድርጅት የሰላም ተልእኮ አንሚ እንዲዘጋ ትናንት ተወሰነ።

የሰላም ጠባቂ ሃይሉን መውጣት ተከትሎ ጦርነት ሊቀሰቀስ ይችላል የሚለው ስጋት እያየለ መጥቶአል።በኒው-ዮርክ የኤርትራ ቋሚ ተጠሪ እንደገለጹት ሃገራቸው ጦርነትን ባትመርጥም፣ግዛቷ የሆነችውን ባድመ በኢትዮጵያ ወረራ ስር መቆየቷን ለመቀበል እንቸገራለን ብለዋል።በሌላ በኩል በቅርቡ መቐለ ውስጥ በተደረገና መለስ ዜናዊ በተገኘበት የሚሊንየም ቀን አከባበር ላይ ጀነራል ሰዐረ መኮንን እንደተናገረው የመከላከያ ሰራዊቱ ከኤርትራ ሊሰነዘር የሚችልን ማንኛውንም ጥቃት ለመመከትና በአነስተኛ ኪሳራ ጦርነቱን ለማሸነፍ ተዘጋጅቷል።

አንዳንድ ተንታኞች ጦርነቱ ከፈነዳ በአፍሪካ ቀንድ አዲስ የሃይል አሰላለፍ ይፈጠራል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።በደቀቀ ኢኮኖሚና በረሃብ ህዝብ እያለቀ ባለበት ሰዐት የሚደረግ ጦርነት የህዝብን አበሳ ከማባባስ ውጭ የሚፈይደው እንደሌለ፣ጦርነቱም ቢነሳ ምንም የህዝብ ተጠያቂነት በሌለው የመለስ መንግስት መመራቱ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል ሲሉ የከዚህ ቀደሙን ስህተት በማስታወስ አንዳንድ ዜጎች ተናግረዋል።

ስለላውና አፈናው ተባብሷል

## “የነፃነት ጥማታችን፤ በደህንነቶች አፈና አይታፈንም”

ከመቼውም ጊዜ በከፋ መልኩ የመለስ አገዛዝ የአፈናና የስለላ መዋቅሩን በመዘርጋት ዜጎችን መውጫ መግቢያ እንዳሳጣና ስርዓቱ ጥላውን የማያምንበት ደረጃ ላይ እንደደረሰ የግንቦት 7 ታማኝ ምንጮች ገለፁ።

ስማቸው ቢገለፅ ጥቃት ይደርስብናል ያሉት እነዚሁ የድርጅታችን ምንጮች እንደገለፁት፤የደህንነት አባላት በግንቦት 97 ምርጫ ጊዜ በቅንጅት መሪዎች ላይ ሲፈፅሙ ከነበሩት ወከባና አፈና ባልተናነሰ መልኩ ፤አሁንም በርካታ ዜጎችን መውጫ መግቢያ አሳጥተዋል።ለአንድ ሰው እስከ አምስትና ስድስት ደህንነቶች ድረስ መመደብ መጀመሩን፣ደህንቶች ተሰባስበው በግለሰቦች ቤት ግቢ እስከማደር መድረሳቸውንና አጠቃላይ የአፈናው መዋቅር በስፋት መዘርጋቱን የገለፁት ምንጮቻችን፤የበርካታ ዜጎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው ሳይቀር በደህንነቶች ክትትል ስር መውደቁን አመልክተዋል።

ወከባው የበዛባቸው ዜጎች፡-”የነፃነት ጥማታችን፤ በደህንነቶች አፈና አይታፈንም”ማለታቸውን የግንቦት 7 ምንጮች ባደረሱን መረጃ አመልክተዋል።

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## “በኢትዮጵያ ረሀቡ እጅግ ከፍቷል።ወደ ሰሜን ምስራቅ ተዛምቷል”

በደቡብ፣በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች የተከሰተው ረሀብ አድማሱንና የጉዳት መጠኑን በማሰፋት ወደ አፋር ክልል መዛመቱን ሴቭ ዘችልድረን ዩኬ ትናንት አሰታወቀ።የድርጅቱ ተወካይ ቻርለስ ማኮርማክ እንዳሉት፤የችግሩና የረሀቡ መጠን የዛሬ አራት ወር ከነበረበት ሁኔታ እጅግ ከፍቷል፤በጣም አስደንጋጭ ሆኗል።በደቡብ ኢትዮጵያ ሰሞኑን ጉብኝት ሲያደርጉ የነበሩት ማኮርማክ፤በአካባቢው ረሀቡ የጉዳቱን መጠን ከማክፋቱም በላይ የረሀብተኞች ቁጥር በአስደንጋጭ ሁኔታ እየጨመረ መጥቷል። “በአካባቢው ብዙ ነገሮች የዛሬ አራት ወር ከነበሩበት ሁኔታ በከፋና ባልተጠበቀ መልኩ ተለውጠዋል።ችግሩ ከምን ጊዜውም በላይ ከፍቷል።በጣምም አስደንግጦኛል”ብለዋል-ተወካዩ። በሽዎች የሚቆጠሩ አጥንታቸው ወደገጽ 2 ዞሯል

## ተ.መ.ድ ወደ ኢትዮጵያ ያስገባው የእርዳታ እህል ተዘረፈ

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የዓለም የምግብ ፕሮግራም ሰሞኑን ወደ ምስራቅ ኢትዮጵያ ለተረጅዎች ያስገባው 1400 ከረጢት እርዳታ እህል መዘረፉን የአካባቢው አስተዳደሮች ገለፁ።የመስተዳድር አካላቱ እንዳሉት፤እህሉን የዘረፉት በአካባቢው የሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች ናቸው።ሆኖም፤ የአካባቢው ሹመኞች አዲጋላ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ተ.መ.ድ ለረሀብተኞች ያስመጣውን እህል ዘርፈዋል የተባሉትን ታጣቂዎች ማንነት ከመግለፅ ተቆጥበዋል።መለስ ዜናዊ በቅርቡ በምስራቅ ኢትዮጵያ ምንም የሚያሰጋ የተደራጁ ሀይላት እንቅስቃሴ የለም ማለቱ ይታወሳል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፤ በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በሚገኙ አንዳንድ ወረዳዎች በተደራጁ ሀይላት ባለፉት ሳምንታት ተጀመሩት የትጥቅ እንቅስቃሴዎች ተጠናክረው እየቀጠሉ እንደሚገኙ የግንቦት ሰባት ዝግጅት ክፍል አስተማማኝ መረጃዎችን በመጥቀስ ዘግቧል።

## “ከእነዚህ አንዱን መሆን ግን የማንነታችን ውጤት ነው”አቶ ኤፍሬም ማደቦ

ግንቦት7ለፍትህ፣ለዲሞክራሲና ለነፃነት ንቅናቄ፤ በዋሽንግተን ዲሲ ባካሄደው ህዝባዊ ስብሰባ ላይ፤የንቅናቄው አባል አቶ ኤፍሬም ማደቦ ካቀረቡት የተሳታፊዎቹን ትኩረት ከያዘ ንግግር፤ ክፍል አንድን ባለፈው እትማችን ማቅረባችን ይታወሳል።ሁለተኛውና የመጨረሻው ክፍል እነሆ፡-“…እኛ የኢትዮጵያ ልጆች ያዋጣናል ብለን በምናምንበት ማንኛውም ዓይነት የትግል ስልት እንጠቀማለን…” ሲሉ ያጀባቸው ጭብጨባው ጋብ ማለቱን ተከትሎ አቶ ኤፍሬም ቀጠሉ፡-.

…ውድ ወገኖቼ ፡ የኢትዮጵያውያን ችግር የሚፈታው በኢትዮጵያውያን ነው።ችግሩ የሚፈታውም እዚያው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው።አገራችን ኢትዮጵያ የጋራ፣ ችግራችን የጋራ፣ጠላታችንም የጋራ ነው። እነዚህ መሰረታዊ ነገሮች ላይ ከተማመንን፤በእኩልነት ላይ የተመሰረተች፣በፍትህ የተሞላች፣ሰብዓዊ መብቶች የሚከበሩባትና ነፃነትና እድገት የሚረጋገጡባትን ኢትዮጵያን መመስረትም የጋራ ሀላፊነት ነው።ታዲያ..ታዲያ ለምን ተደጋግፈን በመቆም ይህችን የምንፈልጋትን ኢትዮጵያን አምጠን አንወልድም?-ሴት ነው የጠፋው?ወይስ ወንድ? ወደገጽ 4 ዞሯል

# ርእሰ አንቀጽ

## የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ጥያቄ፣ የህልውናችን ጉዳይ ነው

በኢትዮጵያ ያለው የሰብአዊ መብትና የፖለቲካ መድረክ መጥበብ በአደገኛ ሁኔታ ላይ መገኘቱን በመጥቀስ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ተቋማት ስጋታቸውን በመግለጫዎቻቸው ይፋ አድርገዋል።ሂዮውማንራይትስ-ዎች በቅርቡ ባወጣው ዘገባ “በኢትዮጵያ የፖለቲካው መድረክ እጅግ እየጠበበና የማያፈናፍን እየሆነ መጥቷል”ሲል፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል በበኩሉም “በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብትና ዴሞክራሲን ማስፈን የማይቻልበት ደረጃ ተደርሷል።የተለያዩ ሃሳቦችንም ማንሸራሸር የማይታሰብ ነው” በማለት ሰጋቱን አጠናክሯል።

በቅርቡ የጸደቀውን የፕሬስ ህግ፣መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶችን ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅና፣የፓርቲዎች ምዝገባና አሰራር ረቂቅ ህግን በዋቢነት ስንመለከት፣ የአገዛዝ ስርአቱ ሃገሪቱን ወደፍጹም አምባገነንነት ደረጃ ለማውረድ ቆርጦ እንደተነሳ ስንናገር የከረምነውን እንድንደግም ያስገድደናል።በአጠቃላይ እየታየ ያለው ሁኔታ፣ በሃገሪቱ፣ ከሰሜን ኮሪያ ጋር በአቻነት የሚተካከል የመንግስታዊ ቁጥጥር አፈና ለማስፈን እየተሰራ እንዳለ እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል።በሃገር ውስጥ “ህግና ደንብ” አክብረው የፓርላማ መቀመጫ አግኝተው የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎችና ግለሰቦች ሳይቀሩ ሰሞኑን የፖለቲካ መድረኩ መጥበብ ከሁሉም በላይ እንዳሳሰባቸው ሲናገሩ እየተደመጡ ነው።አንድ የተቃዋሚ ቡድን መሪ፦ “አሁን ያለው የፖለቲካ መድረክ እየጠፋ መሆኑንና የተቃዋሚ ሃይላትም ለውጥ ለማምጣት ተጽእኖ የማሳረፍ ሃይላቸው ውሱን እንደሆነ” በመጥቀስ “የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ መቀበሪያው ተቆፍሮአል፣መገነዣው ተመቻችቷል፣ግብአተ መሬቱም እየተፈጸመ ነው” በሚል የሰጡት አስተያየት በእርግጥ እመቃው ብልጥ ልጆችንም እንዳላስተረፈ ጥሩ ማሳያ ነው።በዚሁ ላይ በማከልም አንድ ሌላ የፓርላማ አባል አፈናው ቢብስ እንጂ አያንስም በማለት፣ያገዛዝ ስርአቱ ይህን የሚፈጽመው ሳያውቅ ተሳስቶ ሳይሆን በእቅድ በፖሊሲ ደረጃ ታስቦበት እንደሆነም ተናግረዋል።

እንደ ኢትዮጵያ ላለች በተወሳሰበ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግር ለተወጠረች ሃገር፣ ዴሞክራሲ የፍላጎት ብቻ ሳይሆን የመኖርና ያለመኖር ጥያቄም ከሆነ ሰንብቶአል።እንደ ግንቦት 7 ዋነኛ እምነት፣የሃገሪቱ የፖለቲካ ሃይላት ከምንም በፊት ለሁሉም የሚሆን ስርአት የማቆሙን ተግባር ቀዳሚ አጀንዳቸው ሊያደርጉት ይገባል ይላል።ስለ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ስንናገርም፣ ቁልፍ የሆነውን የተቋማት ምስረታ ጥያቄ መልስ ሳይገኝ የሚደረግ ማንኛውም ጥረት ምሉእነት ይጎድለዋል ብለን እናምናለን።ይህ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ጥያቄ አንድ ሰሞን ጫና ሲበዛ የምንጮህለት፣ ሌላ ጊዜ ወደሁለተኛ ደረጃ ጉዳይነት የሚወርድ አይደለም።የስልጣንም ሆነ ሌሎች እንጭፍጫፊ ጉዳዮች ላይ ቀልባችንን በማሳረፍ ከወሳኙ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ማቆም ጥያቄ፣ እኛ ተዘናግተን ህዝብንም እንዳንዘናጋ ስናሳስብ የከረምነውም ለዚህ ነው።

በእኛ እምነት የአንድ ህዝብ መብቱ የሚከበረውና ነጻነቱ የሚረጋገጠው፣ህዝብን በዘላቂነት ተጠቃሚ የሚያደርጉ፣ የመብቱና የሃገሩ ባለቤት እንዲሆን የሚያስችሉ ወሳኝ የስርአት ማቆም ጥያቄዎች መልስ ሲያገኙ ብቻ ነው።አለበለዚያ ማባበያ በሚመስሉ ሽርፍራፊ መብቶች ስንዘናጋ እንደምናየው የአገዛዙ አያያዝ በዚህ ቀጥሎ ሁሉንም መብቶች ወደሚነሳብን መንገድ በማናለብኝነት ከመገስገስ የሚያቆመው አይኖርም።በእኩልነት በማንስተናገድበት ጨዋታ ውስጥ ገብተን በሓዋላ ለሚደርስብን ማንኛውም ችግር ደግሞ፣ፈቃድ ሰጪዎች እኛው እራሳችን መሆናችንንም ማወቅ አለብን።ግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ ዴሞክራሲ የህልውና ጉዳይ በሆነበት፣በዚህ ወሳኝ ወቅት፣የአገዛዝ ስርአቱ በ97ቱ ምርጫ ታይቶ የነበረውን የዴሞክራሲያዊ ስርአት ሂደቱን ቀልሶ አምባገነናዊ ስርአት በመገንባት የተያያዘውን ጥድፊያ አጥብቆ ይቃወማል። ይህን አደገኛ ሂደት ለማስቆም በሚችለው መንገድ ሁሉ አስፈላጊውን ትግል ያደርጋል።ለዚህ የህዝብ መብትና ለሃገር ህልውና መቀጠል ወሳኝ ለሆነው የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ መልስ ለመስጠት፣ ማናቸውንም ተፈላጊ ዋጋ ለመክፈል ያለውን ቁርጠኝነት በድጋሚ ለህዝብ ያረጋግጣል።

**ረሀቡ እጅግ ከፍቷል** ከገጽ 1 የዞረ

የገጠጡና ሞት አፋፍ ላይ የደረሱ ህፃናትን በዐይናቸው እንደተመለከቱ የተናገሩት ሚስተር ማኮርማክ፤ቀደም ሲል በኢትዮጵያ መንግስት 70 ሽህ ህፃናት አስጊ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ቢገለፅም፤ በአሁኑ ጊዜ በሞት አፋፍ ላይ የሚገኙት ህፃናት ቁጥር ከተጠቀሰው አህዝ በጣም እንደሚጨምር ተናግረዋል።

“ረሀቡ ወደ ሰሜኑ ምስራቅ የአገሪቱ ክፍል ስለመዛመቱ የሚያውቁት ነገር ካለ?”ተብሎ ከጋዜጠኞች ለቀረበላቸው ጥያቄም፤ ድርጅታቸው በአካባቢው ባለው ቢሮ አማካይነት ረሀቡ ወደ ሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ እየተስፋፋና የጉዳት መጠኑን እያሰፋ መምጣቱን እንዳረጋገጡ ገልጸዋል-ተወካዩ።አያይዘውም፦“በተለይ በአፋር ክልል አካባቢ ረሀቡ ከፍቷል።ሰውነታቸው ያለቀ በርካታ ህፃናትን ተመልክተናል። የአካባቢው ነዋሪዎች ለክፉ ቀን ይሆነናል ብለው ያጠራቀሙትን ምግብ ጨርሰዋል። በእጃቸው ላይ ምንም የቀራቸው የለም።ከብቶቻቸውም፤ እንደዋልታ ሰውነታቸውን፤ ከግራና ከቀኝ ቆዳቸውን በስተው ሊወጡ የዳዳቸው ታፋዎቻቸው ይታያሉ “ብለዋል።ወገን እያለቀ ዝምታን የመረጡትና በዲ-አፍሪክ ሆቴል ውስኪ ሲራጩ የሚሰነብቱት የክልሉ ባለስልጣናት፤በረሀቡ ጉዳይ ማብራሪያ ይሰጡ ዘንድ በጋዜጠኞች ቢፈለጉም እስካሁን ሊገኙ አልቻሉም። የረሃቡን አስከፊነትና የአገዛዝ ስርአቱ ይህን ለመደበቅ የሚያደርጋቸውን ሙከራዎች ግምት በማስገባት የግንቦት 7 ዜና አውታር ከተለያዩ ምንጮች በማጠናቀር የረሃቡን ዜና አሁንም ይፋ ማድረግ እንደሚቀጥልበት ዝግጅት ክፍሉ በዚህ አጋጣሚ ይገልጻል።

**“ከእነዚህ አንዱን መሆን ግን የማንነታቸን ውጤት ነው”**
ከገጽ 4 የዞረ

’እኔ አንድ ነኝ፣ሁሉን ነገር ማድረግ አልችልም’የሚለው አባባል፤የሞኝና የሰነፍ አባባል ይመስለኛል።ሁሉን ነገር አንተ ብቻ ስራ፤አንች ብቻ ስሪ ያለ የለም።ይህ አይጠበቅባችሁምም!ሆኖም ፤ሁሉን ነገር ያለማድረግ ችሎታችን-አንድ ነገር ከማድረግ ሊወስነን አይገባም።ተግባራችን ወይም ስራችን ሁሌ ደስታን ላያመጣልን ይችላል።ካለተግባር ደግሞ ደስታም፣እፎይታም የለም።ዛሬ ሁላችንም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ አገራችንን ከሚጎዱ ሀይሎች ጋር ተባባሪ እንዳንሆን አደራ እላለሁ። ከሁሉም በላይ ግን በዚህ የሞት የሽረት ትግል ውስጥ፤የመንገድ ዳር ተመልካቾች እንዳንሆን ከልብ አሣስባለሁ።

ውድ ወገኖቼ፣ መንገዳችን እጅግ አድካሚና ውስብስብ ቢሆንም ልባችን -በ እርምጃችን ፤በተስፋና በመርህ የተሞላ ሊሆን ይገባል።መንገዳችን ላይ በሚያጋጥመን እድል ውስጥ ፤ችግር ጎልቶ ሊታየን አይገባም።ይልቁንም እያንዳንዱ ችግር ስለሚያመጣው እድል ልባችን፤’እችላለሁ፣እፈፅማለሁ፣ድል አደርጋለሁ ‘በሚል የፀና ተስፋ ሊሞላ ይገባዋል።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
አምላካችን እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርካት!
አመሰግናለሁ

**ግንቦት 7 ድምጽ በግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን**

**የፖስታ ሳጥን ቁጥር**
POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

# የፖለቲካ ትንተና

በዚህ አምድ ስር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱ መጣጥፎች ይቀርባሉ

## ማነህ ባለ ሳምንት?
## “መንግስታዊ ሽብርተኝነት”ሊቀጣ ይገባል።

ጋቹዬ

መቋጫ ላልተገኘለት የዳርፉር እልቂት፤ ዓለማቀፉ ዓቃቤ ህግ፤የሱዳኑን ፕሬዚዳንት ኦማር ሐሰን አልበሽርን ለመክሰስ መወሰኑን ተከትሎ፤የ”ባለ ሳምንት” አምባገነኖች ሰፈር ሲናጥ ሰንብቷል።በተለየ መልኩ በቅርብ ጊዜ በዜጎቻቸው ላይ የጅምላ ጭፍጨፋ በመፈፀምና የተሸነፉበትን የምርጫ ውጤት በሀይል በመቀልበስ፤በማቆጥቆጥ ላይ ለነበረችው የአፍሪካ ጅምር ዲሞክራሲ ሞት፤ ዋነኞቹ የታሪክም፣ የህግም ተጠያቂ የሆኑት ነፍሰ-ገዳዩ መለስ፣የኬንያው ምዋይ ኪባኪና የዚምባቡዌው ሮበርት ሙጋቤ፤ የጋለ ምጣድ ላይ እንደተንጠባጠበ ቅቤ መንጨርጨራቸውን ቀጥለዋል።

የአፍሪካ መሪዎች ከሁለት ሳምንት በፊት ባደረጉት ስብሰባ፤በሙጋቤ ላይ ጫና የሚፈጥር ጠንካራ አቋም ያሳልፋሉ ተብሎ በዓለማቀፉ ህብረተሰብ ሲጠበቅ፡ መለስና መሰሎቹ በተቃራኒው፤ ከመንታ ወንድማቸው ከሙጋቤ ጎን ቆመው ታይተዋል።ሆኖም የተገረመ የለም።ዛሬም አልበሽር ሲነኩ፦”አሁንስ በዓይናችን መጣችሁብን”ዓይነት ጩኸት ማሰማታቸው፤ አላስገረመንም።ነገ የማን ተራ እንደሆነ ያውቁታልና።የምንገረመው ፤ለማስመሰል ያህል እንኳ ፤ለፍትህ መረጋገጥ መቆማቸውን ለማሳየት ቢሞክሩ ፤ወይም በዓለማቀፉ ዓቃቤ ህግ እንቅስቃሴ ዙሪያ ዝምታን ቢመርጡ ነበር። ግን ግን…እንዴት ፍትህን ይደግፉ? -ራሳቸው ወንጀለኞች ናቸዋ!እንዴትስ ዝምታን ይምረጡ?-እጃቸው በእልፍ ንፁህን ደም ተጨማልቋላ።

‘ደም ያለበት ሰው ይንቀዠቀዣል”ነው ያሉኝ አያቴ?

ባለ ሳምንቱ ቃየል{መለስ}፤የአልበሽርን መከሰስ አስመልክቶ ሰሞኑን የሎስአንጀለስ ታይምስ ጋዜጠኛ ላቀረበለት ጥያቄ፤ክሱን እንደሚቃወመው በመግለፅ ፦*”ለፍትህ የሚሰጥ ትኩረት ሰላምን የሚያሳጣ መሆን የለበትም” ብሏል።*

ይህ ምን ማለት ነው?”አልበሽር ወንጀለኛ ቢሆንም፤እሱን ስትነኩት ሱዳን ትፈራርሳለችና ተውት ፤አትንኩት”መባሉ ይሆን?-ልክ እኛ ከሌለን ኢትዮጵያ ትፈርሳለች “እየተባለ እንደሚዛተው መሆኑ ይሆን?(እንደ አምላክ ሲታዩ የነበሩት ሀይለስላሴም ሄደው አልፈረሰች፤ ሟርተኞች!)

በአምባገነኖችና በዘረኞች ጠማማ መለኪያ ካልሆነ በስተቀር፤ለፍትህ ትኩረት መስጠት ሰላምን በማስፈን ፋንታ ሰላምን የሚያሳጣበት አንዳችም ምክንያት የለም።መለስ ዜናዊ በዓለሙ ፍርድ ቤት ተከሶ ቢቀጣ፤ በየአቅጣጫው ሰላም ያጣችው ኢትዮጵያ፤ እፎይ ብላ ትተነፍሳለች እንጅ፤ምን ታጣለች? በስልጣን ላይ ያለን መሪ የመክሰስ አሰራሩ አዲስና ያልተጠበቀ ከመሆኑ አንፃር ድንጋጤ ፈጥሮ ከሆነ፤አዎ!ማንም ይሁን ማን፤ወንጀልንና ወንጀለኞችን በዓለማቀፉ ችሎት የመቅጣት እንቅስቃሴው እየተጠናከረ መምጣት እንዳለበት ዓለም ተስማምቶበታል።ተስፋ ሰጭ እንቅስቃሴም ተጀምሯል።

“ንጉስ አይከሰስ፤ሰማይ አይታረስ”ለሚለው ብሂል ማን ነበር በዚያ ሰሞን፦”ንጉስም በጥፋቱ ይከሰሳል፡ሰማይም በመብረቅ ይታረሳል”ያለው?

አዎ!ፍትህ ሲዘገይ የቀረ ሊመስል ይችላል።ግን አይቀርም። እስካሁንም ለምን እንደዘገየ ተበዳዩ የኢትዮጵያ ህዝብ፤በዳይ ገዥዎቹም ያውቁታል።መፃኢዉ የዓለማችን ፖለቲካ ግን ‘በፀረ-ሽብርተኝነት ዘመቻ አጋር-ሽፋን፤ መንግስታዊ ሽብርተኝነትን እያስፋፉ ለመጡት ለመለስ ዓይነቶቹ ደም መጣጭ መሪዎች፤ መጫዎቻና መቀለጃ ስፍራ ያለው አይመስልም።”በየአገሮቻቸው ሰብዓዊ መብቶችን የሚጨፈልቁና ዲሞክራሲን የማያከብሩ ሁሉ፤ለፀረ-ሽብርተኝነት ዘመቻው አጋር ሊሆኑ እንዳልቻሉ” ካለፈው ተግባር ተረጋግጧል።ወደፊት ሊሆኑ እንደማይችሉም በሀሳብም፣በመርህም ደረጃ ስምምነት ተደርሶበታል።ተግባሩ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለን እናምናለን።

በእርግጥም እንደመለስ ዓይነቶቹ የዲሞክራሲ ቀንደኛ ጠላቶች ወደስልጣን ከመጡ ወዲህ፤ በየጊዜው ወይም ያለ አንዳች ፋታ የአፍሪካ ቀንድ ሰላም እንዴት እየተበጠበጠና እየተሸበረ እንደሚገኝ ማየቱ ለዚህ ከበቂ በላይ ማስረጃ ነው።እነዚህ አምባገነኖች ፤ አቃዥቷቸው ባደረ ማግስት ፤በቀጥታ ቀጭን ትዕዛዝ አያሌ ንፁህንና ሰላማዊ ዜጎችን አስጨፍጭፈዋል።ዳኝነትን ያህል የተቀደሰ ዙፋን በማርከስ፤”የዓይናቸው ቀለም ያላማራቸውን ” እልፎ ዜጎች በፍትህስምአስረዋል።ገርፈዋል።ገድለዋል።አፈናቅለዋል።ህግን ረግጠዋል።ደም ሊያሰተሰርየው የማይችል ከባድ ወንጀል ፈጽመዋል። የቀንዱን ቀጣናም ሆነ የውስጥ ግዛታቸውን ሲያሸብሩ ከርመዋል።ባጠቃላይ “በፀረ-ሽብር ዘመቻ አጋር” ስም፤ዋነኞቹ አሸባሪዎች ሆነዋል።

ስለዚህም በማቆጥቆጥ ላይ ላሉ ሌሎች አምባገነኖች፤ አስተማሪ ለሆን በሚችል መንገድ ሊቀጡ፤ይገባል።በህዝብና በአገር ጀርባ እንደመዥገር ተጣብቀው ደም እየመጠጡ ዝንተ-ዓለም መኖር የሚመኙትን እነዚህን ስልጣን ናፋቂ ወንጀለኞች፤ በማያዳግም ሁኔታ መቅጣት፤ለአካባቢያችንና ለአህጉራችን ከዚያም አልፎ ለዓለማችን ሰላም፤ወለል ያለ ጥርጊያ መስራት ይሆናል።

ግንቦት 7 ለፍትህ፣ለዲሞክራሲና ለነፃነት ንቅናቄ፤በሰው ልጆች ላይ የተፈፀሙ መንግስታዊ የጅምላ ግድያ ወንጀሎች፤በዓለማቀፉ ችሎት ፊት መቀጣት አለባቸው ብሎ አጥብቆ ያምናል።ግፈኛውን የመለስ አገዛዝ ለማንበርከክ ከሚያደርገው ትግል በተጓዳኝ፤ እንደ መለስ ዓይነቶቹ ወንጀለኞችና ተባባሪዎቻቸው በሚቀጡበት አሰራር ዙሪያ የዓለሙ ዐቃቤ ህግና ፍርድ ቤት እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ በሚችለው አቅም ጥረት ያደርጋል።ተግቶ ይንቀሳቀሳል።በእዚህ ዙሪያ ከሚሰሩ ዓለማቀፍ የሰብዓዊ መብት ተቋማትና አገር በቀል ድርጅቶች ጋር ይተባበራል።መረጃዎችን አሰባስቦ ለሚመለከታቸው አካላት ይልካል።እነዚህ ደም መጣጮች፤ሩቅ ባለሆነ ጊዜ ውስጥ የዘሩትን እንደሚያጭዱም በእርግጠኝነት ያምናል።

ለምን ፅሁፉን በዳርፉር አማፅያን መሪ ንግግር አይዘጋም?

በአልበሽር መከሰስ ዙሪያ የነ መለስን መንጫጫት የተመለከቱት የአማፅያኑ መሪ ሚስተር አሊ ፦”አልበሽር፤የእነዚህን መሪዎች ድጋፍ ማግኘታቸው የሚገርም አይደለም።መሪዎቹ የሱዳንን ህዝብ ወደው ወይም ለአልበሽር ተቆርቁረው ሳይሆን፤በየራሳቸው እጅ ላይ የብዙ ንፁህን ደምና አጥንት ዋጋ ስላለባቸው ነው”ነበር ያሉት።

“ማን ነህ ባለ ሳምንት?
ያስጠምድህ ባ’ስራ ስምንት”

# ሃይለ ሀሳብ

በዚህ አምድ ስር የተለያዩ ነጻነትንና ትግልን የተመለከቱ ጉዳዮች ይስተናገዳሉ

## “ከእነዚህ አንዱን መሆን ግን የማንነታቸን ውጤት ነው”አቶ ኤፍሬም ማደቦ

ከገጽ 1 የዞረ

ሆኖም፤ የአንዱን የኢትዮጵያ ክፍል ችግር ከሌላው ኢትዮጵያዊ ችግር ነጥለን መፍታት እንደማንችል ሁሉ፤ህዝብን ከህዝብ ነፃ አውጥተን የህዝብን ችግር መፍታትም አንችልም።ኢትዮጵያ በምትባለዋ አገር ውስጥ የሚኖረው የእያንዳንዱ ግለሰብና ማህበረሰብ መብትና ሙሉ ነፃነት እስካልተከበረ ድረስ፤አገራችን ኢትዮጵያ ነፃ አገር ልትባል አትችልም።እኔ ያንተን ነፃነት እንደኔ ነፃነት ካላየሁት፤አንተም የኔን ነፃነት እንዳንተ ነፃነት ካላየኸው፤ሁታችንም ነፃነት አይኖረንም።

ስለዚህ ዛሬ፤’የእዚህ ነፃ አውጭ፤የእዚያ ነፃ አውጭ’ የምንባል ድርጅቶች፣ፓርቲዎች፣የፖለቲካና የሲቪክ ተቋማት፣ በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን ሁላችን፤ አገራችንን ከተበላሸ ስርዓት፣ከድህነት፣ከሁዋላ ቀርነት፣ከበሽታና ከረሀብ ነፃ ማውጣት ይኖርብናል።የጠላቶችችን አንዱና ዋነኛው ጥንካሬ፤ የኛ መነጣጠል ነው። ዛሬ እያንዳንዳችን ምንም ያህል ጠንካራ ብንሆን፤በተናጠል ማሸነፍ ስለማንችል፤በጋራ ጠላታችን ላይ በጋራ እንነሳ!ስል ጥሪ አደርጋለሁ።በጋራ እንታገል ሲባል ከዚህ ቀደም እንዳደረግነው በጅምላ ተገናኝተን ገና ከጅምሩ የተሰናከለ ባቡር ላይ እንሳፈር ማለት አይደለም።በጋራ ስንል፤ ራዕያችን፣አላማችንና ፍላጎታችን ተመሳሳይ ሊሆን ይገባል ማለታችን ነው።’ስትራቴጂያችን ምን ይሁን?’በሚለው ላይ ልንለያይ እንችላለን።መለያየትም አለብን።አሸናፊ ስትራቴጂ የምናገኘው ልዩነቶቻችንን ጨምቀን ነውና።ን

ግግሩ፣ውይይቱ፣ኮምፕሮማይዝ መደራረጉ እዚህ ላይ ነው የሚመጣ::ዲሞክራሲያዊ ህብረተሰብ በመገንባቱ ረገድ ብዙ የምንለያይ አይመስለኝም።ልዩታችንን የምንገነባው ‘ዲሞክራሲው ምን ዓይነት መልክ ይኑረው?’በሚለው ጥያቄ ላይ ነው።እንግዲህ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት፤ውይይታችን እንዲህ ዓይነቱን ልዩነት ነው የሚፈታው።ዋናውና ትልቁ ቁም ነገር፤በዲሞክራሲ ማመንና ይህ የሚገነባው ዲሞክራሲ፤ትናንት ኢትዮጵያ፣ዛሬም ኢትዮጵያ፣ነገም ኢትዮጵያ ተብላ በምትታወቀው በዚያች ከሰሜን ኢኳቶር 3 ዲግሪ ላይበምትገኘው አገር ውስጥ መሆን አለበት የሚለው ነው።ለእኔ፣ለአንተ፣ ለአንች፣ለእናንተ፣ ለእኛና ኢትዮጵያ ውስጥ ላለው 80 ሚሊዮን ህዝብ፤ኢትዮጵያ ሲባል የሚሰማንና የሚታየን አንድና ተመሳሳይ ነገር ሊሆን ይገባል።የፖለቲካ ስልጣን ፤ሆዳቸውን ብቻ ከሚያመልኩ ስስታሞች እጅ ‘በእንካችሁ ተቀበሉን መልክ አይወጣም።ወጥቶም አያውቅም።እነዚህንስስታሞች በሚገባቸው ቋንቋ ልናናግራቸው ይገባል። ማሸነፍ ፤ፍላጎቱ ብቻ ስላለን የሚሆን ነገር አይደለም።ማሸነፍ ህይወታችንን ሙሉ የምናደርገው ያላሰለሰ ትግል ውጤት ነው።አሸናፊ ለመሆን ብቻ የተፈጠረ ሰው እንደሌለ ሁሉ፤ሁሌም ተሸናፊ ለመሆን ከእናቱ ሆድ የወጣ የለም።ከእነዚህ አንዱን መሆን ግን የማንነታችን ውጤት ነው።ዛሬ፤የማንነታችንም ሆነ ድል የማድረግ አቅማችን ትልቁ መለኪያ ድርጅታዊ ብቃታችን ነው።

ጠንካራ፣በእቅድ የሚመራ፣ስራዎችን በተቀነባበረ መልኩ የሚሰራና ዲሲፕሊንድ የሆኑ አባላት ያለው ድርጅት ሳይኖረን ስለማሸነፍ ማውራት አንችልም።ድርጅት፤ነገና ከነገ ወዲያ እንገነባለን እያልን የምናስተላልፈው ሳይሆን ለነገ የሚያበቃን ሀይል ነው።በቀድሞ የድርጅት ታሪካችን ድርጅትን በተመለከተ የነበረብን ትልቁ ችግር፤ከተደራጀን በሁዋላ ለተደራጀንበት ዓላማ ትልቅ ቦታ በመስጠት ፋንታ ዋናውን ትኩረታችንን ለራሱ ለድርጅቱ መስጠታችን ነው።ሌላው ችግራችን ደግሞ የድርጅት መሪዎችን ከድርጅት በላይ፤ድርጅትን ደግሞ ከ አገር በላይ እነመለከት ነበር።ይህ አመለካከት ማክተም አለበት።ድርጅት፤መረማመጃ መንገድ እንጅ በራሱ ግብ አይደለም።

ወገኖቼ፤ ጊዜ፣ሁኔታና ጠላቶቻችን ሲለዋወጡ፤እንዲሁም ችግር ፊታችን ላይ ሲደቀን የትግል ስልታችንና ችግሮችን የምናስወግድበት መንገድ መለዋወጥ አለበት።ደግሜ እላለሁ፦የማይለወጠው የማንነታችን መገለጫና መለኪያ የሆነውመርሃችን ብቻ ነው።ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው መንግስት በአመጽ ስልጣን ላይ የመጣ፣ከግንበት 97 ምርጫ በሁዋላ ደግሞ በአመጽ ስልጣን ላይ የቆየ፣በአጠቃላይ በአመጽ የሚያምን መንግስት ነው።ይህ መንግስት የተጠናወተውን አመጽ፤ከኛም ሆነ ከውጭው ዓለም ሊደብቀው የሚሞክረው በተለመደው ውሸቱ ነው።ዕውቁ ሩሲያዊ የስነ-ፅሁፍ ሰው አሌክሳንደር እንደተናገሩት፤አመጽ የሚሰፍነው ፤ውሸትን በመደርደር ብቻ ነው።ሁሌ እንደተዋሸ መኖር የሚቻለው ደግሞ በአመጸ ብቻ ነው።ስለዚህ ይህን በአመጸ በውሸት የተሞላ መንግስት አምስት ዓመት እየጠበቅን በራሱ ሜዳ፣ራሱ ባረቀቀው የጨዋታ ህግ፣ራሱ በሰየመው ዳኛና በራሱ ተመልካች ፊት አሸንፋለሁ ማለት፤በመኪና ጨረቃ ላይ ለመድረስ-ከናሳ(NASA) ጋር እንደመወዳደር ነው።

ውድ ኢትዮጵያውያን! የድሮው ታሪካችን ብዙ ቁስል ነበረበት።ፊት ለፊት የሚጠብቀን ግን ብሩህና የተሻለ ጊዜ ነው።አንድ ነገር አስረግጬ መናገር የምችል ይመስለኛል፦በታሪክ ወደ ሁዋላ ሄደን አዲስ ጅምር መጀመር አንችልም።ግን ሁላችንም የትናንቱን ይቅር ተባብለንና ዛሬ አዲስ ጅምር ጀምረን የምንፈልጋትን ኢትዮጵያን መገንባት እንችላለን።ሁላችንም እንደምንገነዘበው አብዛኛው የ አገራችን የፖለቲካ ትግል የተመራው፤በምሁሩ ክፍል ነው።በከፍተኛ ደረጃ መማር በራሱ፤ሁላችንን መሪ አያደርገንም-መልካምና ታማኝ ተከታዮች እንድንሆን ይረዳናል እንጂ። መሪነት፤ሃላፊነት ወይም በሹመት የሚደረስበት ደረጃ አይደለም።ይህንን በሚገባ ካልተረዳን፤ሁላችንም በየደረጃው መሪዎች መሆናችን ይጠፋንና ነገራችን ሁሉ የተበላሸ ይሆናል።መሪ፤ብቁ ተከታዮችን አይፈራም-ብዙ መሪዎችን እንጂ።መሪ፤በህዝብ ላይ መከራ አያበዛም-መከራን ይጋራል እንጂ።መሪ፤ ለህዝብና ለአገር ይቆጣል እንጂ-በ ህዝብና በአገር ላይ አይቆጣም።የመሪ ጥሪት፤ ለዝናና ከመቃብር በላይ ለሚቀር ታሪክ አይደለም።የመሪ ጥሪት፤ ስራውና ልፋቱ በህዝብ ህይወተወ ውስጥ ዘልቆ እንዲገባና እሱ ያየውን ህዝብ እንዲያይ ማድረግ ነው።

ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኞቼ!

ዛሬ እያንዳንዳችን ሁለት ምርጫ አለን።አንድ-እየበሉ መኖርና ማለፍ;።ሁለት- አገራችንን ከ አደጋ ማዳን።አገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ ከሩቅ ለሚመለከታት የምታሳዝን፣ቀርቦ ላያት የምታስለቅስ፣ለሚኖርባት ደግሞ የምድር ሲዖል ሆናለች።ይህ ሁሉ የሆነውና እየሆነ ያለው፤ጠላቶቻችን ክፉዎች፣አመፀኞችና ጨካኞች ስለሆኑ ብቻ አይደለም።እኛም የኢትዮጵያ ልጆች በምናደርጋቸውና በማናደርጋቸው ነገሮች የተነሳ ነው።እኔ አንድ ነኝ፣ሁሉን ነገር ማድረግ አልችልም’የሚለው አባባል፤የሞኝና የሰነፍ አባባል ይመስለኛል።ሁሉን ነገር አንተ ብቻ ስራ፤አንች ብቻ ስሪ ያለ የለም። ወደገጽ 2 ዞሯል